“እናትና ልጅ” ከተባለው የውድአላት ገዳሙ
የግጥም መድብል የተወሰዱ ግጥሞች

## ጅሎ

ተው ብትል አይሰማት - ሞኙ እየቦረቀ፣
ህመሙን ቁብ ሳይል - በጣሯ እየሳቀ።
የእማማውን ወተት - የርሐቡን መጋኛ፣
ሰው የመሆኛውን - የነፍሱን መዳኛ፡
ባልተወለደ አንጀት - ጨምቆ እያፈሰሰ፣
በሁለት እጆቹ - ጡቷን እያረሰ፣
ቁልቁል እየሳባት - እስከሚሆን አልቦ
‘ሻሞ’ ይላቸዋል - ልጆቹን ሰብስቦ።
ጅል!

(ታህሳስ 06/96)

* <<ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል>> እንዲባል

## የረጋ ... ?

አየህ!
ምን መሰለህ ...

ይ - ሁ - ን ብለህ ከረጋህ፣
መደላድል መሆን ነው ዕጣህ፣
የሌሎች ጓዝ መጫኛ፣
የዕድል በራቸው መገኛ።

አስተውል!
ወተትም'ኮ ቢረጋ፣
ከወዲያ ወዲህ ካልተላጋ፣
ከመሆን በቀር ኮምጣጣ፣
ቢሹት ቅቤውም አይወጣ።

(ሚያዚያ 07/96)

*እንደራስ እምነት እንጅ እንደሌሎች እምነት ላለመኖር ተጠንቀቅ!

## ወይ መውደድ!

<<ይህን ካላመጣህ ዞረ በል ከፊቴ እኔ አልፈልግህም>>
ስትለው አምርራ <<እኔ እወድሻለሁ ነፍሴ ነሽ>> ይላታል፣
በእግሯ እየረገጠች በጥፊ ስትከድነው፣
ጉንጩን ያብስና ስቆ አይኗን ያያታል፣
<<ይኼኔ እኔ ብሆን>> ብዬ እስከምቀና፣
እሱው ተበድሎ አቅፎ ይስማታል፣
እፍኝ ሙሉ አቧራ ባይኑ ስትሞጅር፣
እምባ እያፈሰሰ ዝም አላት ታግሶ፣
በሷው ይብስና ጮሃ ስታለቅስ አባበላት ዳብሶ፣
ጊዜ ዕድሜን አድሏት ሁሉን እስክታውቀው፣
እስከዚያው ይቻላት፣
አባቷ ነውና መቼስ ምን ያድርጋት።

(ሚያዚያ 28/96)

## ከየት መጣህ ደሞ?

የነፍሴ 'ንጉርጉሮ - ሚሾና ድርደራ
የዕድሜ ልኬን ፀፀት - የሕልሜን ሙሽራ፡
ፍራጅ ተቀምጬ - ሐዘኔን አምርሬ፣
እንባዬን አፍስሼ - አልቅሼ ቀብሬ።
እንዳይጠብህ ብዬ - የአካሌ መድረኩ፣
መኖሪያ ሰጥቼህ - መጥኜ በልኩ፡
ከተቀበርክበት - ከልቤ ናስ ወጥተህ፣
ባይን ባይኔ ልትዞር - ደሞ ከየት መጣህ?

(ጥቅምት 28/96)

**_Back to Meskot_**

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot*. ***You may contact Wudalat Gedamu for comments at*** *wudalatgedamu@yahoo.com* ***or by writing to Wudalat Gedamu, P.O.BOX 34137 Addis Ababa, Ethiopia.***